የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

# የተሽከርካሪ ክብደትና መጠንን መወሰኛና መቆጣጠሪያ

## መመሪያ ቁጥር_________/2017

**መጋቢት 2017 ዓ.ም**

## መመሪያ ቁጥር---- 2017

# የተሽከርካሪ ክብደትና መጠንን መወሰኛና መቆጣጠሪያ መመሪያ

የመንገድና የትራንስፖርት ዘርፍ ልማት በሀገሪቱ በመካሄድ ላይ ያለውን ሁሉን አቀፍ ልማት ለማፋጠን ከፍተኛ እገዛ ከሚያደርጉ የመሠረተ ልማት ዘርፎች ዋነኛና ቁልፍ የልማት ዘርፍ ከመሆኑም በላይ በመንግሥት ትኩረት የተሰጠበት ዘርፍ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የመንገድና የትራንስፖርት ዘርፍ ልማት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቅ እንደመሆኑ በከፍተኛ ወጪ የለማውን ሃብት በአግባቡ የመጠበቅ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም፡፡ ይህ ከመንገድ ሀብት ጥበቃ አኳያ ሲታይ በከፍተኛ ወጪ የተገነቡ መንገዶች በዲዛይናቸው መሰረት ሊያስተናግዱ ከሚገባቸው ክብደት በላይ በጫኑ ተሽርካሪዎች አማካኝነት ጉዳት እንዳይደርስባቸው መከላከል እና የመንገዶችን የጂኦሜትሪክ ዲዛይን መሰረት የትራፊክ ፍሰት ሳይስተጓጎል መንገዶች ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግን ይመለከታል፡፡

ይህንንም ትርጉም ባለው መልክ እውን ለማድረግ የተሽከርካሪዎችን ክብደትና መጠንን መወሰንና ተሽከርካሪዎች በህግ ከተወሰነው የከብደትና መጠን ወሰን በላይ እንዳይሆኑ፣ የተሽከርካሪዎች ክብደትና መጠንን ለመወሰንና ለመቆጣጠር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 491/2014 በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደንብ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን "አህጉራዊና ቀጠናዊ ስምምነቶችን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፣ በተለይም ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት "የሰስትዮሽ ትራንስፖርት እና ትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም" ማለትም የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ገበያ (ኮ.ሜ.ሳ.)፣ የምስራቅ አፍሪካ ማሕበረሰብ (ኢ.ኤ.ሲ.) እና በደቡባዊ አፍሪካ ልማት ማሕበረሰብ (ሳ.ዲ.ክ.) መካከል በመንገድ ትራንስፖርት ትስስርን ለማሳለጥ የተደረገ ስምምነትን ታሳቢ በማድረግ የፀደቀ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ የተሽከርካሪዎች ክብደትና መጠንን መወሰኛና መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 491/2014 ፀድቆ መተግበር ከጀመረ በኋላ በትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ክፍተቶችን ለማስተካከል፣ በአንዳንድ አንቀጾች የተቀመጡ ሃሳቦችን ከተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ኢትዮጵያ አባል ለመሆን በሂደት ላይ ካለችው እንደ የዓለም የንግድ ድርጅት ከሚከተሉት አለም አቀፋዊ አሰራሮች ጋር ለማጣጣም፣ ደንቡን በቀጥጣ በሚያስፈፅሙት በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር፣ በኢትየጵያ መገዶች አስተዳደር እና የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራዝ መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር፣ ደንቡን ከሚያስፈፅሙት አካላት በተጨማሪ በቁጥጥር ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ሚና በሚኖራቸው ባለድርሻ አካላት ማካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለመፍጠር፣ የመንገድ መሰረተ ልማቶችንና የሎጅስቲክ ስርዓቱን በተጣጣመ መልኩ ለማሳለጥ እና በደንቡ መሠረት እንደ ሀገር ወጥ የሆነ አሠራር በመዘርጋት በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ርዝመት፣ ስፋት፣ ከፍታ እና ክብደት በተሳካ ሁኔታ ለመቆጣጠር በደንብ ቁጥር 491/2014 አንቀጽ 10 እና 23 የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሽከርካሪ ክብደትና መጠንን መወሰኛና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር ________/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

በደንቡ ላይ የተጠቀሰው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ደንብ"** ማለት የተሽከርካሪዎችን ክብደትና መጠንን ለመወሰንና ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 491/2014 ማለት ነው።
2) **"መጠን"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ ሊኖረው የሚገባ የጎን ስፋት፣ ርዝመት እና ቁመትን የሚገልጽ ማብራሪያ ነው፤
3) **"መንገዱን የሚያስተዳድረው አካል"** ማለት እንደ የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ እና መሰል መንገዶችን ለማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጣቸውን ተቋማት ያካትታል፤
4) **"አደገኛ ጭነቶች"** ማለት ተሽከርካሪዎች ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ዕቃዎችን በሚያጓጉዙበት ወቅት በፍተሻ የሚካሄድ ከሆነ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ማለትም ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ኬሚካሎች እና በሰው፣በተሽከርካሪ እና በአከባቢ ተፅዕኖ የሚያደርሱ የሚጎዱ ጭነቶችን ያካትታል።
5) በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተደነገገዉ የሴትንም ጾታ ያካትታል።

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ሀ) በደንቡ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው አግባቦች የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

1) ይህ መመሪያ በማናቸውም የኢትዮጵያን መንገድ በሚጠቀሙ ክብደታቸው ከ3,500 ኪሎ ግራም በላይ በሆነ እና በሰዓት ከ20 ኪ.ሜ በላይ በመንገድ ላይ በሚሽከረከሩ ተሽከርካሪዎች፣ የተጣመሩ ተሽከርካሪዎች እና ተሣቢዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።
2) የተፈጥሮ አደጋ መከላከል እና በድንገተኛ አደጋ የወደሙ መሰረተ-ልማቶችን በመገንባት ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚንቀሳቅሱ ተሽከርካሪዎች ከፍቃድ ሰጪው አካል የአደጋውን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ እና በፍቃድ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣ የተፈጥሮው አደጋ አይነት በሀገር ደረጃ የደረሰ እና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የሚፈልግ መሆን አለበት፣
3) ኢትዮጵያ በተፈራረመቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ማለት ኢትዮጵያ እንደሀገር የተፈራረመችው እና አባል የሆነችባቸው ያካትታል፣

ለ) በደንቡ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1-8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) መንገዱን የሚያስተዳድረው አካል በደንቡም ሆነ በዚህ መመሪያ በህግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል የተሰጠው መብትም ሆነ ኃላፊነት በሚያስተዳድራቸው መንገዶች ላይ ተሰጥቶታል፣

# ክፍል ሁለት

# የተሽከርካሪ ክብደትና መጠን አወሳሰንና ቁጥጥር

## 4. ስለ መመርመሪያ እና መመዘኛ መሣሪያዎች

በደንቡ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ የሚሸፈን ማንኛውንም መመርመሪያ ወይም መመዘኛ መሣሪያን ለመጠቀም መሣሪያውን ብቃት ባለው ባለሙያ/ድርጅት አስፈትሾ በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የወጡ አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶችን ማሟላቱ ሲረጋገጥ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ፈቃድ ያገኛል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመመርመሪያ ወይም የመመዘኛ መሣሪያን የሚጠቀም ማንኛውም ሰው በዓመት አንድ ጊዜ የደረጃ መስፈርቱን በማሟላት በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ፈቃዱን ማሳደስ አለበት።
3) ማንኛውም መመርመሪያ ወይም መመዘኛ መሣሪያ ልኬትን የሚያዛቡ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወይም ጥቆማ ሲቀርብ ወይም ጥገና ከተደረገለት በኋላ በድጋሚ በባለሙያ አስፈትሾ ፈቃዱ እንዲታደስ ይደረጋል።
4) አገልግሎቱን በሚሰጡ በሁሉም ሚዛን ጣቢያዎች የመመዘኛ መሳሪያው በአግባቡ እንደሚሰራ የሚያረጋግጠውን ፍቃድ ወይም ሰርተፍኬት ለተጠቃሚው በሚታይ ቦታ ላይ መስቀል ይኖርበታል።

## 5. የተሽከርካሪን ክብደት እና መጠን ስለመወሰን

በደንቡ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) ማንኛውም የተሽከርካሪ ገጣጣሚ፣ አምራች ወይም አስመጪ ሀገር ውስጥ የተገጣጠሙ ሆኑ የተመረቱ ወይም ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎች በዚህ ደንብ የተደነገገውን የክብደት እና መጠን ወሰኖች መሰረት መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ አገልግሎት ማዋያ ፈቃድ ጠይቆ ማስመዝገብ ይኖርበታል።
2) ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሽከርካሪዎች የምዝገባ መስፈርትም ሆነ በምዝገባ ወቅት በደንብ ቁጥር 491/2014 መሠረት የሚፈቀድ የተሽከርካሪ አጠቃላይ ርዝመት፣ ስፋት፣ ከፍታ እና የአክስል መሸከም አቅም በግልጽ ማስቀመጥ እና ማረጋገጥ ይኖርበታል።
3) ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ በቴክኒክ መመርመሪያ ቼክሊስት ውስጥ በደንቡ ላይ የተጠቀሱት የተሽከርካሪ የተፈቀደ አጠቃላይ ርዝመት፣ የጎን ስፋት፣ ከፍታ እና ክብደት ተካቶ ተሽከርካሪው በዚህ መሠረት እንዲመረመር በማድረግ፣ ተሽከርካሪዎች በዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ መሰረት ጠቅላላ ክብደትና የመሸከም አቅም በየዓመቱ መታደስ ይኖርበታል።

## 6. የተፈቀደ መጠን

ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም፡-

1) የተሽከርካሪ፣ የተሳቢ ወይም የግማሽ ተሳቢ ጠቅላላ የጎን ስፋት ከፊት የውጭ በኩል ከቀኝ ጠርዝ እስከ ግራ ጠርዝ ወይም በተቃራኒው ተለክቶ ከ2.65 ሜትር መብለጥ የለበትም፤
2) የተሽከርካሪ፣ የተሳቢ ወይም የግማሽ ተሳቢ ጠቅላላ ከመንገድ ከፍታው ጭነቱን ጨምሮ ከ4.60 ሜትር መብለጥ የለበትም፤
3) የማናቸውም ተሽከርካሪ፣ ያልተጣመረ ነጠላ ባለሞተር የፊትና የኋላ መከላከያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ከፊት ጠርዝ እስከ ኋላው ጠርዝ ከ12.50 ሜትር መብለጥ የለበትም፤
4) የተጣመረ ተሽከርካሪ ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከነተሳቢው የፊትና የኋላ መከላከያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ከፊት ጠርዝ እስከ ኋላው ጠርዝ ከ18.5 ሜትር መብለጥ የለበትም፤
5) ማናቸውም ተቀጣይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ጠቅላላ ርዝመት ከ22 ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡

## 7. ስለተቀጣይ ተሽከርካሪዎች

ማናቸውም ተቀጣይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ተቀጣጥለው ለመጓዝ የሚፈቀድላቸው፡-

1) የሚስበው ተሽከርካሪ እና አንድ ወይም ሁለት ተሳቢዎች፤
2) አንድ ተሽከርካሪ ሌላ ተሳቢ ካልሆነ ተሽከርካሪ ጋር ሲቀጠል፤
3) በአደጋ ወይም በብልሽት ጊዜ ከአንድ ተሽከርካሪ ጋር ሌላ ተሳቢ ያልሆነ ባለሞተር ተሽከርካሪ እና ተሳቢ ሲቀጠሉ ይሆናል፡፡

## 8. ከተሽከርካሪ አካል ውጭ የሚውል ጭነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) ለማንኛውም ሰው ጭነቱ ከተሽከርካሪው ፊት እና ከበስተኋላው መጨረሻ ካለው አካሉ 1.25ሜትር በላይ የሆነ ጭነት የጫነን ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡
2) ለማንኛውም ሰው ጭነቱ ከተሽከርካሪው የቀኝ ወይም የግራ ጎን ካለው አካል 15 ሴንቲ ሜትር (0.15 ሜትር) በላይ የሆነን ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡

## 9. በመንገድ ላይ እንዲያርፍ የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት

1) በደንቡ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ) ከባለሶስት አክስል በላይ የሆነ ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መንገዶች ሲንቀሳቀስ ቢገኝ የተሽከርካሪው ባለቤት በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በደንቡ አባሪ 1 መሰረት የተቀመጠውን ከፍተኛ ቅጣት ድምር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ጭነቱንም በሌላ በመንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ በተፈቀደለት ተሽከርካሪ መገልበጥ ይኖርበታ፣

**2)** በደንቡ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 6 ሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚፈቀድ የትርፍ ክብደትን በሚመለከት በሚከተለው መሰረት ይሆናል፣

ሀ) የሚፈቀድ የክብደት መጠን የተለያዩ የተሽከርካሪዎች ዓይነቶችን ከግምት በማስገባት 12 ፐርሰንት ቶሌራንስ የተፈቀደ ይሆናል። አጠቃላይ የአክስል ድምር ስድስት ላላቸው ተሽከርካሪ 400 ኩንታል እንዲጭኑ ይፈቀዳል። ለነጠላ አክስል ወይም አክስል ክፍል በደንቡ ከተፈቀደው ከፍተኛ የክብደት መጠን በላይ እስከ 12% ትርፍ ሊጭን ይችላል፣

**1)** ለመሪ አክስል የተፈቀደ ክፍተኛ ከብደት 8.96 ቶን

**2)** ለነጠላ አክስል የተፈቀደ ክፍተኛ ከብደት 11.2 ቶን

**3)** ለጥንድ አክስል የተፈቀደ ክፍተኛ ከብደት 20.16 ቶን

**4)** ለባለሶስት አክስል የተፈቀደ ክፍተኛ ከብደት 26.88 ቶን

ለ) ለተሽከርካሪዎች ወይም ለተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች በደንቡ ከተፈቀደው ከፍተኛ ክብደት 56 ቶን መጠን በላይ እስከ 12% ትርፍ ሊጭን ይችላል፣

**1)** ለተሽከርካሪዎች ወይም ለተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች የተፈቀደ ክፍተኛ ከብደት 62.72 ቶን

**3)** በደንቡ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1-3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የሚፈቀደው ከፍተኛ ክብደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚፈቀድ የትርፍ ክብደትን ታሳቢ በማድረግ ከሚከተሉት ትንሹ ይሆናል፣

ሀ) ከፍተኛ የተፈቀደ የአክስል ወይም የአክስል ክፍል ድምር፣
ለ) በደንቡ አንቀጽ 9 መሰረት የተወሰነ ከፍተኛ የተፈቀደ ክብደት፣
ሐ) በደንቡ አንቀጽ 10(1) መሰረት በስሌት የተገኘ ከፍተኛ የተፈቀደ ክብደት፣
መ) 56 ቶን፣

# ክፍል ሶስት

## የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

በደንቡ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1-8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

### 10. የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር

1) ከውጭ ወደ ሀገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ማስገቢያ ማሳወቂያ መስፈርት በአዲሱ ደንብ ቁጥር 491/2014 መሠረት እንዲሆን በመስፈርት ማሳወቂያ ላይ የሚፈቀድ የተሽከርካሪ አጠቃላይ ርዝመት፣ ስፋት፣ ከፍታ እና የአክስል መሸከም አቅም በግልጽ ያስቀምጣል፣
2) ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት ምንም አይነት የደንቡንም ሆነ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚጥስ ተሽከርካሪዎች የስፖንዳ ስፋት አለመኖሩን ማረጋገጥ እና ይህንንም በዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት በማረጋገጥ በየዓመቱ ያድሳል፣
3) ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ በቴክኒክ መመርመሪያ ቼክሊስት ውስጥ በደንቡ ላይ የተጠቀሱት የተሽከርካሪ የተፈቀደ አጠቃላይ ርዝመት፣ የጎን ስፋት፣ ከፍታ እና ክብደት ተካቶ ተሽከርካሪው በዚህ መሠረት እንዲመረመር ማድረግ፣ ይህ ካልሆነ የተሰጠውን ፍቃድ በታየው ለውጥ መሰረት ያስተካክላል፣
4) የአክስል ክብደትና መጠን ቁጥጥር እና አጠቃላይ የትራንስፖርት ስርዓቱን ለማስፋፋትና ለማሻሻል ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና የሕግ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣
5) በደንቡ መሰረት የተቀመጠውን የጭነት ገደብ ታሳቢ በማድረግ የጅምላ ጭነቶችን ለማጓጓዝ ደንቡ ላይ የተቀመጡትን ወሰኖች የሚያሟሉ ተጨማሪ ተሽከርካሪዎች እንዲሰማሩ ያደርጋል፣
6) የአክስል ክብደትና መጠን ቁጥጥር ሂደትን ለማሻሻል ደንብ እና መመሪያዎችን ማሻሻል፣
7) የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ ኦፐሬተሮች ግንዛቤ ይሰጣል፣
8) በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠም የትርፍ ጭነት ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣
9) የጭነት ተሽከርካሪዎችን ምልልስ ለማሳደግ እና የሎጅስቲክስ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ በሀገራችን ቁጥጥር በሚደርግባቸው ሚዛን ጣቢያዎች የዴመሬጅ አዋጅ እስታንዳርድን እንዲተገበር ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣
10) ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር እና ከኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ የሚቀርብለትን በደንቡ አባሪ አንድ ላይ የተዘረዘሩትን የቅጣት መጠን የክለሳ ጥያቄ ያፀድቃል፣
11) የተከለሰ የቅጣት መጠን በደብዳቤ ያሳውቃል፣ ተግባራዊ መደረጉን በመመዘኛ ጣቢያው እና በተቋማቱ ድህረ ገጽ ላይ መለጠፍ ያረጋግጣል፣

12) የተለያዩ አካላት በተናጥል ከሌሎች አገራት ጋር የሚያከናውኑት የንግድ ስምምነቶች ከመፈረማቸው በፊት ከደንቡም ሆነ ከዚህ መመሪያ ድንጋጌ ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፣

## 11. የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

1) የተሽከርካሪዎች ክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን በዘመናዊ መልኩ ያቋቁማል እንዲሁም ያሻሽላል፣
2) የተሽከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር ስርዓትን በማዘመን እና ዘመናዊ የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎችን ያስተዋውቃል፣ ይተገብራል፣ያስተሳስራል፤
3) የትርፍ ጭነት በመንገድና ድልድይ ሀብት ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳትን በመተንተን የውሳኔ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
4) የኢትዮጵያን መንገዶችና ድልድይ ዘመኑ ከሚያመርታቸው ተሽከርካሪዎች ጋር የተጣጣመ የመሸከም አቅም እንዲኖራቸው በጥናት ያደርጋል፣ያቀርባል፤ይገነባል ፤
5) በደንቡ አባሪ አንድ ላይ የተዘረዘሩትን የቅጣት መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በመደበኛ አክስል በኪሎ ሜትር ያለውን ወጪ በማስላት በዓመት አንድ ጊዜ የመከለሻ የውሳኔ ሃሳቦችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፣ በፀደቀው መሰረት ይፈፅማል፣

## 12. የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ

1) የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ በክፍያ መንገዶች አዋጅ ቁጥር 843/2006 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ መሠረት በተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና መጠንን ለመወሰንና ለመቆጣጠር የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 491/2014ን እና ይህንንም መመሪያ በሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶች ላይ ያስፈፅማል፣
2) የተሽከርካሪዎች ክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን በዘመናዊ መልኩ ያቋቁማል እንዲሁም ያሻሽላል፣
3) የተሽከርካሪዎች ክብደት ቁጥጥር ስርዓትን በማዘመን እና ዘመናዊ የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎችን ያስተዋውቃል፣ ይተገብራል፣ያስተሳስራል፤
4) የትርፍ ጭነት በመንገድና ድልድይ ሀብት ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳትን በመተንተን የውሳኔ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
5) በደንቡ አባሪ አንድ ላይ የተዘረዘሩትን የቅጣት መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በመደበኛ አክስል በኪሎ ሜትር ያለውን ወጪ በማስላት በዓመት አንድ ጊዜ የመከለሻ የውሳኔ ሃሳቦችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፣ በፀደቀው መሰረት ይፈፅማል፣

## 13. የከተማና መሠረተልማት ሚኒስቴር

1) ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እና በመቀናጀት ይሰራል፣
2) ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፣

## 14. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

1) ሚኒስቴሩ የሚያከናውናቸው የኢንዱስትሪ ስራዎች በደንብ ቁጥር 491/2014 እና በዚህ መመሪያ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ፣
2) የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ጥሬ ዕቃዎች በሚገቡበትም ሆነ ምርቶች በሚላኩበት ወቅት በተፈቀደ የተሽከርካሪዎች ክብደትና መጠን አስተካክለው

እንዲጨኑ ግንዛቤን ይፈጥራል፣

3) የማኑፍክቸሪንግ ዘርፍ ከክብደትና መጠን ጋር የሚያጋጥማቸውን ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣
4) ከመንገዶች አስተዳደር፣ ከክፍያ መንገዶች ኢንተረፕራይዝ እና ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር ጋር ከአምራች ኢንዱስትሪው ከውጭ የሚያስገባቸውን ጥሬ እቃዎች ለሚቀርብለት ጥያቄ በማጣራት ምላሽ ይሰጣል፣
5) የተለያዩ አካላት በተናጥል ከሌሎች አገራት ጋር የሚያከናውኑት የንግድ ስምምነቶች ከመፈረማቸው በፊት ከደንቡም ሆነ ከዚህ መመሪያ ድንጋጌ ጋር እንዲጣጣሙ ያደርጋል፣

## 15. ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

1) በተሽከርካሪዎች የሚከናወኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች በደንብ ቁጥር 491/2014 እና በዚህ መመሪያ መሰረት እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
2) የተለያዩ አካላት በተናጥል ከሌሎች አገራት ጋር የሚያከናውኑት የንግድ ስምምነቶች ከመፈረማቸው በፊት ከደንቡም ሆነ ከዚህ መመሪያ ድንጋጌ ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፣
3) ማንኛውንም አስጫኝ ተሽከርካሪው ከመነሻው ጭነቱን በደንቡ እና በዚህ መመሪያ መሰረት አስተካክሎ እንዲነሳ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፣
4) ማንኛውንም አስጫኝ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተጣለበትን ግዴታ እየተወጣ መሆኑን ያረጋግጣል፣
5) መመዘኛ እና መመርመሪያ መሣሪዎች በስታንዳርዱ መሠረት ጊዜውን ጠብቀው ካሊብሬት በማድረግ ሰርተፊኬት መስጠት እና መቆጣጠር፣
6) የካሊብሬሽንን በወቅቱ ማከናወን አስፈላጊነት በመገንዘብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣
7) የሦስትዮሽ ትራንስፖርት እና ትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም መፈጸምን ይከታታላል፣

## 16. የጉሙሩክ ኮሚሽን

1) ማንኛውንም አስጫኝ ተሽከርካሪው ከመነሻው ጭነቱን በደንቡ እና በዚህ መመሪያ መሰረት አስተካክሎ እንዲነሳ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፣
2) በጉምሩክ ጣቢያዎች ላይ የቁጥጥር ሂደቱን ያግዛል፣
3) በጉምሩክ የታሸጉ የኮንቴነር ጭነቶችን፤ ጭነቱን ለማስተካከል ከባለንብረቶች ትብብር በተጠየቀ ጊዜ ተገቢውን ትብብር ያደርጋል፣

## 17. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን

1) የተሽከርካሪዎችን ክብደትና መጠንን ስርዓቱን በማገዝ ደንቡንም ሆነ ይህንን መመሪያ ያስከብራል፣
2) የህግ አካላትን በጣቢያዎች ላይ በመመደብ የቁጥጥር ስርዓቱን ያግዛል፣
3) የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ደንቡን የጣሱ አካላት ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እና በጋራ ይሰራል፣

## 18. የተሽከርካሪ ባለቤቶች ግዴታዎች

1) የተሽከርካሪ ባለቤቶች በደንቡ ላይ በተደነገገው መሠረት የተጣለባቸውን ግዴታዎች መወጣት አለባቸው፣
2) የተሽከርካሪ ባለቤቶች የተጣለባቸውን ቅጣት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ካልከፈሉ በደንቡ የተቀመጠው ቅጣት እንደተተበቀ ሆኖ የዲሜሬጅ ሕግ ተግባራዊ ይደረጋል፣

## 19. የተሽከርካሪ አስመጪዎች፣ ገጣጣሚዎች እና አምራቾች ግዴታዎች

1) ማንኛውም የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም አምራች በዚህ ደንብ የተሸፈነን ማንኛውንም ተሽከርካሪ አገልግሎት ላይ ከማዋሉ ወይም እንዲውል ከማድረጉ በፊት የተሽከርካሪውን ክብደት እና መጠን በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ማስመዝገብ አለበት፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት አንድ ተሽከርካሪ ለምዝገባ ሲቀርብ ሚኒስቴሩ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ወይም ተሽከርካሪውን የሚመዘግበው አካል የተሽከርካሪው ክብደት እና መጠን በዚህ መመሪያ ከተገለፀው የክብደትና የመጠን ወሰን ካልበለጠ ብቻ ነው፣
3) ሚኒስቴሩ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) መሠረት ተሽከርካሪውን ከመመዝገቡ በፊት የተሽከርካሪውን ክብደትና መጠን ወሰን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከተሽከርካሪው አምራች የሚቀርበውን የቴክኒክ መመዘኛ ማንዋል እና ስፔሲፊኬሽን መሠረት ሊያደርግ ይችላል፣

## 20. መልቲ-ሞዳል ድርጅት

1) ለሁሉም ትራንስፖርተሮች በዚህ ደንብ መሰረት ጭነቶችን አስተካክለው እንዲጭኑ ማድረግ፣
2) የመልቲሞዳል ጭነቶችንም ከሚዛን ጣቢያ ህጎች ጋር ተጣጥመው እንዲታሸጉና ይህንኑ ጭነት በሚጭኑ ተሽከርካሪዎች ላይ ከተፈቀደላቸው የአክስል ክብደት መጠን በላይ እንዳይሆኑ ማድረግ፣

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. ቅጣት እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች

ሀ) ቅጣት

በደንቡ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1-7፣ አንቀጽ 15 እና አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1-6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) ከባለሶስት አክስል በላይ የሆነ ተሽከርካሪ ቀደም ብለው ደምቡ ከመሻሻሉ በፊት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች በልዩ የመንግስት ውሳኔ ሲገቡ ምዝገባ በልዩ ሁኔታ በሚኒስትሮች ውሳኔ ሊስተናገድ ይችላል።
2) ከባለሶስት አክስል በላይ የሆነ ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መንገዶች ሲንቀሳቀስ ቢገኝ የተሽከርካሪው ባለቤት በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በደንቡ አባሪ 1 መሰረት የተቀመጠውን ከፍተኛ ቅጣት ድምር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ጭነቱንም በሌላ በመንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ በተፈቀደለት ተሽከርካሪ መገልበጥ ይኖርበታል፣
3) በደንቡ አባሪ አንድ በየ400 ኪ.ግ የክብደት ጭነት ጭማሪ ውጪ ለተገኙ የሚዛን ልኬቶች የተጓዳኝ የቅጣት ተመኖች በውስጠ ግምት ሂሳብ ቀመር እየተሰላ ክፍያው እንዲፈጸም ይደረጋል፣
4) የተሽከርካሪ ክብደትን በመተላለፍ ለተቀመጡ ቅጣቶች የሚከፈል ክፍያ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ወይም መንገዱን ለሚያስተዳድረው ህጋው አካል የሚከፈል ይሆናል፣
5) በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ወይም መንገዱን የሚያስተዳድረው አካል ከክብደት በላይ ጭነት ለሚከፈል ቅጣት በደንቡ እና በዚህ ድንጋጌ መሰረት በሚታተም ቅጽ ወይም ወደፊት በስርዓት በሚመቻች የክፍያ ደረሰኝ መስጠት ይኖርበታል፣
6) በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ወይም መንገዱን የሚያስተዳድረው አካል ከክብደት በላይ ጭነት ቅጣት መክፈያ መንገድ ወይም ቦታ ሊያመቻች ይችላል፣
7) ማንኛውም በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ወይም መንገዱን የሚያስተዳድረው አካል የክብደት መመዘኛ ጣቢያዎች ሳይመዘን ያመለጠ ተሽከርካሪ ትርፍ ጭነት ይዞ ከተገኘ በደንቡ የተጣለበትን የትርፍ ጭነት ቅጣቱን በሁለት ተባዝቶ እንዲከፍል ተደርጎ ጭነቱን እንዲያስተካክል ይደረጋል።

ለ) አስተዳደራዊ እርምጃዎች

በደንቡ አንቀጽ 12 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) በሌላ ህግ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም የተሽከርካሪ ክብደትን በሚመለከት ደንቡም ሆነ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው የክብደት መጠን ወሰን በላይ የሆነ ተሽከርካሪ ወይም ተጣማሪ ተሽከርካሪ ከመጠን በላይ የሆነውን ጭነት እስኪያስተካክል ወይም ወደሌላ ተሽከርካሪ እስኪቀንስ ድረስ ተሽከርካሪው ተይዞ ይቆያል።
2) የተቀጣ ኦፕሬተር ቅጣቱን ከፍሎ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነዱን እስከሚያቀርብ ድረስ መንጃ ፍቃድ እና የተሽከርካሪዉ ሊብሬ ተይዞ ይቆያል፣

### 22. ልዩ ፈቃድ

በደንቡ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1-9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ላይ ከተቀመጠው ውጪ ክብደትን በተመለከተ የሚቀርብ የልዩ ፈቃድ ጥያቄ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ወይም ለመንገዱ አስተዳዳሪ ብቻ የሚቀርብ ሲሆን፣ መጠንን በተመለከተ ለሚኒስቴሩ ብቻ መቅረብ ሲኖርበት፣ ለቀረቡት ጥያቄዎች በተመሳሳይ ምላሽ ይሰጣል፣
2) ክብደት እንዲሁም መጠንን በተመለከተ ለሚቀርቡ የልዩ ፍቃድ ጥያቄዎች የመንገድ እና ድልድይ ደህንነት ባገናዘበ መልኩ በቴክኒካል ጥናት ላይ ተመስርቶ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፣
3) በነጠላ ለሚጓዝ ተሽከርካሪ ልዩ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው በጭነቱ ልዩ ባህርይ ምክንያት መነጣጠል የማይችል ጭነት ለማጓጓዝ አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚገጥምበት ወቅት ነው፣
4) የልዩ ፍቃድ ጥያቄ በሚፈቀድበት ወቅት በደንቡ አባሪ አንድ የተቀመጠውን ዝቅተኛ ቅጣት ድምር ለአገልግሎት ይከፍላል፣
5) የልዩ ፍቃድ ጥያቄ የሚቀርበው ተሽከረካሪው በጭነት መነሻ በታው ላይ ሆኖ እና ጉዞ ከመጀመሩ በፊት መሆን ይኖርበታል፣
6) የመመዘኛ ጣቢያ ላይ ተይዞ ለሚገኝ ተሽከርካሪ የሚሰጥ የልዩ ፈቃድ ምላሽ አይኖርም፣
7) ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው ያልተለመደ ጭነት ተሸክሞ ሲንቀሳቀስ የተገኘ ተሽከርካሪ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ወይም በመንገዱ አስተዳዳሪ ተይዞ እንዲቆይ ይደረጋል፣ በደንቡ አባሪ አንድ የተቀመጠውን ከፍተኛ ቅጣት ድምር ይከፍላል፣
8) በልዩ ፍቃድ ለሚጓዙ ተሽከርካሪዎች በጉዞ ወቅት ለሚደረጉ እጀባዎች እና መንገድ ላይ ለመጓዝ የሚያስፈልጉ ማንኛውም ወጪዎች በተሽከርካሪው ወይም በጭነቱ ባለቤት ይሸፈናል፣

### 23. ቁጥጥር ስለማድረግ

በደንቡ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1-3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ወይም የመንገዱ አስተዳዳሪ ተንቀሳቃሽ የክብደት መመዘኛ ጣቢያ የማቋቋም እንዲሁም በመንገድ አውታር ወይም መመዘኛ ጣቢያ ላይ የክትትል ቴክኖሎጂ በመጠቀም ቁጥጥር ማድረግ ይችላል፣
2) ከክብደት በላይ የተጫነ ጭነት በመመዘኛ ጣቢያ ማራገፍ አይፈቀድም ጭነቱ ሊስተካከል የማይችል ከሆነ ኦፕሬተሩ ጭነቱን ለመቀነስ ሌላ ተሽከርካሪ ማዘጋጀት አለበት፣
3) ኦፕሬተሩ ከክብደት በላይ የተጫነውን ጭነት ወደ ሌላ ተሽከርካሪ ለማራገፍ በተመዘነበት ጣቢያ የማቆያ በታ ከሰስት ቀናት በላይ መቆየት አይችልም። ከተጠቀሰው ቀን በላይ የቆየ ከሆነ የዲሜሬጅ አዋጅ ተግባራዊ ይደረግበታል።

4) ከክብደት በላይ የጫነ ተሽከርካሪ አደገኛ እቃዎችን መጫኑ ከተረጋገጠ እና ጭነቱን ወደ ሌላ ተሽከርካሪ የማራገፍ ሂደቱ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ በደህንነት ባለሞያ ከተረጋገጠ የተቀመጠውን ቅጣት አራት እጥፍ እንዲከፍል ተደርጎ በልዩ ሁኔታ እንዲያልፍ ሊደረግ ይችላል፣

## 24. የመለካት ሥርዓት

በደንቡ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1-4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1) አንድ ተሽከርካሪ በደንቡ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ተመዝኖ ክብደቱ ከመጀመሪያው መመዘኛ መሳሪያ ንባብ የተለየ ከሆነ በመጀመሪያው እና በሁለተኛው የምዘና ንባብ ልዩነት መሰረት የቅጣት መጠኑ ተሰልቶ በሁለቱ ቅጣት መካከል ያለውን ልዩነት እንዲከፍል ይደረጋል፣
2) ከአንድ አክስል በላይ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ተመዝነው በእያንዳንዱ አክስል የተገኘው የሚዛን ውጤት ተደምሮ የተሽከርካሪው የአክስል ስብስብ ውጤትን ሊሰጥ ይችላል፣
3) በአንድ የሚዛን ጣቢያ ላይ ተመዝነው በዚህ ደንብ እና መመሪያ መሰረት መሆናቸው ተረጋግጦ ለመመዘናቸው ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ያለፉ የኮንቴይነር ጭነቶችን የጫኑ ተሽከርካሪዎች በሌላ ተመሳሳይ የሚዛን ጣቢያዎች ላይ ማረጋገጫቸውን ብቻ በማሳየት ማለፍ ይችላሉ፣

## 25. ክልከላዎች

በደንቡ ላይ የተደነገጉት ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለማንኛውም አካል የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1) ለማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው ክብደት ወይም መጠን በላይ የሆነ ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ ማሽከርከር ወይም እንዲሽከረከር ማድረግ፤
2) ማንኛውም ሰው በመንገድ ላይ ከባለሦስት አክስል በላይ የሆነ አክስል ያለውን ተሽከርካሪ ማሽከርከር፤
3) በዚህ መመሪያ የሚሸፈን ማንኛውንም መመርመሪያ ወይም መመዘኛ መሣሪያን ለመጠቀም መሣሪያውን ብቃት ባለው ባለሙያ አስፈትሾ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስትቲዩት የወጡ አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶችን በማሟላት ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ፈቃድ ሳይወስድ መገልገል፤
4) ማንኛውም አካል በደንቡም ሆነ በዚህ መመሪያ ከተደነገገው የክብደትም ሆነ የመጠን ወሰን ውጪ በልዩ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ ከተመለከተው አሰራር ውጪ፣ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብም ፈቃድ መጠየቅም አይችልም፤
5) በዚህ መመሪያ ውስጥ በተለይ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንም ሰው በማንኛውም መንገድ ላይ ክብደቱ በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተወሰነው በላይ የሆነን ማንኛውንም ተሽከርካሪ መንዳት ወይም ማንቀሳቀስ፤ ወይም ለተሽከርካሪው ባለቤት ተሽከርካሪው እንዲንቀሳቀስ ወይም ተነድቶ እንዲሄድ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 26. የመተባበር ግዴታ

1) ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 27. የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት

1) ኦፐሬተሮች ወይም ባለንብረቶች ያላቸዉን የአሰራር ሥርዓት ቅሬታ ወይም እርምት እንዲደረግባቸዉ የሚያስፈልጉ የአሰራር ክፍተት ካጋጠማቸዉ በየሚዛን ጣቢያው በተቀመጡ የሃሳብ መስጫ ሳጥኖች ወይም አስተዳደሩ በሚያስቀምጣቸዉ ሌሎች አማራጮች አስተያየታቸውን መግለፅ ይችላሉ፣
2) የሃሳብ መስጫ ሳጥኖቹ በየአካባቢው በሚገኙ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶች በየወቅቱ ይከፈታሉ፣ የተሰጡት አስተያየቶች ተመርምረው አስፈላጊው ማሻሻያ ወይም የእርምት እርምጃ ይወሰዳል፣
3) ተሽከርካሪዉ ሲመዘን ከክብደት በላይ ጭነት ተገኝቶበት በተመዘገበው የምዘና ክብደት ቅሬታ ያለዉ ኦፕሬተር፣ የጭነት ወይም የተሽከርካሪ ባለንብረት፡-
   ሀ) ኦፕሬተሩ ተሽከርካሪውን ከሚዛን ጣቢያው ሳያወጣ ማቆም እና የክስ ፓድ ላይ አለመፈረም ይኖርበታል፣
   ለ) ኦፕሬተሩ ወይም ባለንብረቱ ቅሬታውን ለሚዛን ጣቢያ ኃላፊው በማመልከት ከኃላፊዉ ጋር በጋራ በመሆን ተሽከርካሪውን በድጋሚ ማስመዘን እና ክብደቱን ማረጋገጥ ይችላል፣
   ሐ) በሚዛን ጣቢያ ኃላፊ በቂ ምላሽ አልተሰጠኝም የሚል የቅሬታ አቅራቢ የተሽከርካሪውን ሠሌዳ፤ የሚዛን ጣቢያውን ስም እንዲሁም ቁጥጥሩ የተከናወነበትን ሰዓትና የደረሰውን ችግር በመግለጽ ቅሬታው በቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶች ይህንን ጉዳይ እንዲከታተል ኃላፊነት ለተሰጠዉ የሥራ ክፍል ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፣
   መ) በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ቅሬታው እንደደረሰው በፍጥነት ጉዳዩን አጣርቶ ለቅሬታ አቅራቢው ተገቢዉን ምላሽ ይሰጣል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣
4) ቅሬታ አቅራቢዉ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ 3 በተቀመጠዉ መሰረት ችግሩ አልተፈታልኝም ብሎ ካመነ በሀገሪቱ ህግ መሰረት በመደበኛ ፍርድ አቤቱታዉን ማሰማት ይችላል፣

## 28. ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

## 29. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሊያሻሽለዉ ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

## 30. መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ------ ቀን ---- /2017 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ዶ/ር አለሙ ስሜ**

**የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**